በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

# ቅዳሴ ቤት ተከበረ።

## በኖርዌይ ቴሌማርክ እና ቬስትፎልድ የበዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤት ተከበረ።



በኖርዲክ እና ግሪክ ሀገረ ስብከት በኖርዌይ የበዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤት በአረጋዊው የሀገረ ስብከታችን ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ኤልያስ ቡራኬ፣ የጣልያን እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ሕርያቆስ በተገኙበት መስከረም 3፣ 2019 ዓ.ም. ተመርቀ። በዚህ ታሪካዊ ክብረ በዓል ላይ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ካህናት፣ ዲያቆናት እና ከተለያዩ ከተሞች የተሰበሰቡ ሕዝበ ክርስቲያን በተገኙበት በፍጹም መንፈሣዊ ሥነ ሥርዓት በድምቀት ተከብሯል።








የበዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በ2014 ዓ.ም. (2022) በብጹዕ አቡነ ኤልያስ ቡራኬ ተቋቋመች። ቤተ ክርስቲያናችን በአለፉት አራት ዓመታት በርካታ አገልግሎቶችን ስትሰጥ የቆየች ሲሆን፣ አጥቢያው የራሱን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ለመግዛት ባደረገው ጥረት፣ በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ፣ በእመቤታችን ድንግል ማርያም አማላጅነት ግንቦት 2018 ዓ.ም. ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ለመግዛት ተችሏል።

የተገዛው ሕንጻ ከአሁን በፊት **Sion - ጽዮን** በሚል ስያሜ የሚጠራ ሲሆን በአካባቢው 'የጽዮን ሕንጻ' በመባል ይታወቃል። ብጹዕ አባታችን አቡነ ኤልያስም የቦታውን አቀማመጥ እና የሕንጻውን ታሪክ በመመርመር የቤተ ክርስቲያናችንን ስያሜ ደብረ ጽዮን በዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ብለው ሰይመዋታል።



> ብጹዕ አባታችን ‘ቤተ ክርስቲያን መግዛት ብቻ ሳይሆን ሕጻናትን በማስተማር ሰንበት ትምህርት ቤቱን በማደራጀት ጠንክራችሁ እንድትሰሩ’ በማለት ማሳሰቢያ፣ ቃለ ምዕዳን እና ቡራኬ ሰጥተዋል።

ታቦተ ሕጉ ከመንበሩ ተነስቶ ፣ በካህናት እና ምእመናን ታጅቦ ሥርዓተ ዑደት ከተደረገ በኋላ፣ በዓሉ በጸሎት ተፈጽሟል።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር።**

**ደብረ ጽዮን በዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን**
ቴሌማርክ እና ቬስትፎልድ ፣ ኖርዌይ

Hellestvedtveien 12, 3965 Herre
eotctv7@gmail.com